የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የአፋር ክልል ዲንካራ ጋዜጣ

AFAR REGION DINKARA GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

አስራ አንደኛ ዓመት ቁጥር 69
ሠመራ ቀን 2004 ዓ.ም

በአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት ምክር ቤት
ጠባቂነት የወጣ

11th year No 69
Samara-, 2012

ማውጫ

የ xÍR ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የጤና አገልግሎት አሰጣጥና አስተደደር አዋጅ..... ገጽ 1

አዋጅ ቁጥር 69/2004 ዓ.ም.

የ xÍR ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የጤና አገልግሎት አሰጣጥና አስተደደር አዋጅ

የ xÍR ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃውን የጠበቀ እና በስርዓት የሚመራ እንዲሆን ለማስቻል በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የጤና ተቋሞች አንድ ወጥ በሆነ የአመራር፤ የአሰራርና የክትትል ሥርዓት እንዲመሩ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ፤

የጤና አገልግሎት ተቋማት የአገልግሎት ጥራትና ብቃት በማጠናከር አዲስ ስለሚከሰቱ በሽታዎች ተገቢውን ቅድመ ጥንቃቄ፤ አፋጣኝ ምላሽና ለዚሁ የሚሆን የመረጃ ሥርዓትና አቅም እንዲኖር ለማስቻል፤

የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞችን አደረጃጀትና የሥራ አመራር ማሻሻል፤ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት እንዲሁም መንግሥታዊ ካልሆኑ የጤና ተቋሞች ጋር ያላቸው ግንኙነት ሕጋዊ መሰረት እንዲኖራቸው ሁኔታዎችን ማመቻቸት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በ xÍR ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ም/ቤት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 47 ንዑስ አንቀፅ 3(ሀ) መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የ xÍR ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጤና አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 69/2004" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ

1) "ክልል መንግሥት" ማለት የ xÍR ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ማለት ነው፣
2) "ቢሮ" ማለት እንደ አግባቡ የ xÍR ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጤና ጥበቃ ቢሮና በሥሩ በየደረጃው ያሉትን የጤና መምሪያና ጽ/ቤትን የሚያጠቃልል ነው፣
3) "የመማክርት ጉባኤ" ማለት ከተለያዩ አግባብ ካላቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋሞች በሚወከሉ አባላት የሚቋቋምና በጤና አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር ለጤና ቢሮ የአማካሪነት ሚና ያለው አካል ነው።
4) "የሆስፒታሎች የስራ አመራር ቦርድ" ማለት በመንግሥት ሆስፒታሎች የተለያዩ አግባብነት ያላቸውን አካላት በአባልነት የሚያቅፍ ሆኖ የሆስፒታሉን አጠቃላይ የሥራ አመራር እቅድና በጀት በበላይነት የሚወስንና የሚመራ አካል ነው።
5) "የሆስፒታሎች ሥራ አመራር" ማለት በመንግሥት ሆስፒታሎች አግባብ ካላቸው ክፍሎች የሚውጣጡ አባላት ያሉበት የሆስፒታሉን የዕለት ተዕለት ሥራና እንቅስቃሴ በበላይነት የሚመራና የሚከታተል አካል ነው።
6) "የመሰረታዊ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋም ስራ አመራር" ማለት በመንግስት መሰረታዊ ጤና አገልግሎት መስጫ ተቋም ደረጃ አግባብ ካላቸው የሥራ ክፍሎች የተውጣጡ አባላት ያሉበት የመሠረታዊ ጤና ተቋማትን የዕለት ተዕለት ሥራና እንቅስቀሴ በበላይነት የሚመራና የሚከታተል አካል ነው።
7) "የመንግስት ጤና ተቋም" ማለት በክልሉ መንግሥት ሥር የሚተዳደር ሆስፒታል፣ ጤና ጣቢያ፣ጤና ኬላ ማለት ነው።
8) "የግል ጤና ተቋም" ማለት በጤና ዘርፍ ከመንግሥት መዋቅር ውጭ በግል የጤና አገልግሎት እንዲሰጥ ፈቃድ የተሰጠው የግል ድርጅትን ያጠቃልላል፣
9) "መንግስታዊ ያልሆነ ጤና ተቋም" ማለት በጤና ዘርፍ ከመንግስት መዋቅር ውጭ የጤና አገልግሎት እንዲሰጥ ፈቃድ የተሰጠው አትራፊ ያልሆነ ተቋም ነው፣
10) "የጤና አገልግሎት" ማለት የበሽታ መከላከልንና ቁጥጥርን፣ ጤና ማጎልበትን፣ የተላላፊ በሽታዎች ቅኝትን፤ የአካል፣ የላብራቶሪ፣ የራጅና ሌሎች ጤና ነክ ምርመራዎችን፣ የፈውስ ሕክምናን፣ የጤና አጠባበቅ ትምህርቶችን ያጠቃልላል።
11) "የአስቸኳይ ጊዜ ወይንም ድንገተኛ የጤና አገልግሎት" ማለት በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ክስተቶች ምክንያት ሕዝብ ለተላላፊ በሽታዎች ሲጋለጥ የሚሰጥ የጤና አገልግሎት ነው።
12) "ወረርሽኝ" ማለት ከተቀመጠለት የዓለም አቀፍ መስፈርት በላይ በማንኛውም በሽታ ዓይነት የተጠቁ ሰዎች ቁጥር በዝቶ ሲታይ ነው፣
13) "ገቢ" ማለት የጤና ተቋማት ከሚሰጧቸው ማናቸውም የጤና አገልግሎቶች፤ የመድሃኒት ሽያጭ፤ ከሌሎች አገልግሎቶች እና ንብረቶች ሽያጭ የሚያገኙት ገቢ እንዲሁም በዓይነትም ሆነ በጥሬ ገንዘብ የሚያገኙት እርዳታ ነው፤
14) "ክፍያ የማይጠየቅበት የጤና አገልግሎት" ማለት የጎበረተሰቡን የጤና አጠባበቅ ልምድ ከማሳደግ እንዲሁም በሕዝብ ጤና አጠባበቅ ጉልህ ጠቀሜታ ያላቸውን የጤና አገልግሎቶች ከመስጠት ጋር በተያያዘ ለሁሉም የጎበረተሰብ ክፍል ያለክፍያ የሚሰጥ አገልግሎት ነው፤

15) “የመጣሻ ክፍያ” ማለት አንድ ሰው በመሠረታዊ ጤና አገልግሎት ተቋም የሚችለውን አገልግሎት ሊያገኝ ሲችል ከደረጃው በላይ ወደሆነ ተቋም ሲጠይቅ እንዲከፍል የሚጠየቀው ተጨማሪ ክፍያ ነው፤

16) “የነፃ ሕክምና” ማለት ወደፊት በደንብ በሚወሰነው መሠረት ወጪው አግባብ ባለው አካል ተሸፍኖ የሚከፈል ለዜጎች በነፃ የሚሰጥ የጤና አገልግሎት ነው

17) “ወጪውን የሚሸፍን አካል” ማለት የመክፈል አቅም ለሌላቸው ወይም ለሌሎች የጎብረተሰብ ክፍሎች የሚወጣውን የጤና ወጭ የሚሸፍን ማለት ነው

18) “የጤና መድኅን” ማለት የአገልግሎት ተጠቃሚዎችን ወጪ በሦስተኛ ወገን የሚሸፍን የመንግስት ወይም የግል ድርጅት ማለት ነው።

19) “ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ማለት ነው፣

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በክልሉ ውስጥ በሚገኙ ሆስፒታሎች እና ጤና ጣቢያዎች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>የጤና አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር</u>

4. <u>የጤና አገልግሎት አሰጣጥ መርህ</u>

1) የ KLI# መንግሥት የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች የጤና አገልግሎት የሚሰጡት የክልሉ ቢሮ የሚወስነውን ክፍያ በማስፈጸም ይሆናል፤

2) ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም ሰው የሚከፍለው በማጣቱ ምክንያት በመንግስት ጤና ተቋማት የጤና አገልግሎት ከማግኘት አይከለከልም

3) የክልሉ መስተዳድር በሚያወጣው ደንብ መሠረት የነፃ ሕክምና ማስረጃ የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው ነፃ የሕክምና አገልግሎት ሊያገኝ ይችላል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፤

4) የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት በዕቅድ ዝግጅታቸውና የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የጎብረተሰብ ተሳተፎን ማረጋገጥ አለባቸው።

5) ማንኛውም የመንግሥትም ሆነ የግል ጤና ድርጅት ቅድመ ክፍያ ሳይጠይቅ ድንገተኛ የጤና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት

6) ማናቸውም የጤና አገልግሎት በመስጠት ተግባር ላይ የሚሰማራ ሰው ወይም ድርጅት ከቢሮው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሳያገኝ ሥራ መጀመር አይችልም

5. <u>የጤና አገልግሎት አደረጃጀትና አስተዳደር የሥልጣን አካላት</u>

የ xÍR ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የጤና አገልግሎት አስተዳደር የስልጣን አካላት

1) የጤና ቢሮ
2) የመማክርት ጉባኤ
3) የሆስፒታሎች የሥራ አመራር ቦርድ
4) የሆስፒታሎች የሥራ አመራር
5) የመሰረታዊ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት የሥራ አመራር ናቸው።

6. <u>የጤና ቢሮ ሥልጣንና ተግባር</u>

የክልሉን አስፈጻሚ አካላት ስልጣንና ተግባር ለመወሠን ተሻሽሎ በወጣው አዋጅ ቁጥር 55/2003 በአንቀፅ 20 ለጤና ቢሮ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል።

1) የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች ሊኖራቸው የሚገባውን የሰው ኃይል ብዛት፣ ብቃትና ስብጥር፣ የሕንጻ፣ የሕክምና መሣሪያዎች እና የመገልገያዎች ደረጃ ይወሥናል፣

2) የመንግስት የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት አመራር አካላት በሚያቀርቡት ሀሳብ መሠረት ለሚሰጡት የጤና አገልግሎት ሊከፈል የሚገባውን ክፍያ የተቋማቱን ወጪ እና የሕዝቡን የመክፈል አቅም ከግምት ውስጥ ማስገባቱን በማረጋገጥ መርምሮ ያጸድቃል፣
3) የመንግስት የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት የሰው ኃይል፤ ብቃት፣ የአሰራር ሥርዓት፣ ድርጅታዊ አቅም እንዲጠናከር ተገቢውን እገዛ ያደርጋል፣
4) የጤና ተቋማትን ደረጃ መለየት የሚያስችል የመመዘኛ መመሪያ ያወጣል፤ በዚህም መሠረት ለጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ደረጃ ይሰጣል፣
5) በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የመንግሥት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የግል የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት የሚሰጡ ስለ/መሆኑ ይቆጣጠራል፣
6) የጤና አገልግሎት ለማስፋፋትና ጥራቱንም ለማሻሻል የወጡ ልዩ ልዩ መሥፈርቶች፣ መመሪያዎችና ደንቦች በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል
7) ቢሮው ማንኛውም የጤና ባለሙያ ወይም ድርጅት የሙያ ሥነ ምግባር መጠበቁን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ የማይፈጽም ሲሆን እርምጃ ይወስዳል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፣
8) ቢሮው ከግሉና ሌሎች መንግሥታዊ ካልሆኑ በጤና ዘርፍ ከሚሠሩ ድርጅቶች ጋር የጤና ተቋማት እንዲስፋፉና የአገልግሎታቸው ጥራት እንዲሻሻል የቴክኒክ እገዛ ያደርጋል፣
9) በቢሮው የሚደረጉ የሥልጠናና የአሰራር መመሪያዎች ዝግጅት ላይ የግሉ ዘርፍ እንዲሳተፍ ያደርጋል፣
10) ቢሮው በተለያዩ ደረጃ የሚገኙ የጤና አገልግሎት የአመራር አካላትና የጤና ድርጅቶች አደጋ ከመድረሱ በፊት ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል የመረጃና የሎጂሲቲክ አቅም እንዲገነባ እንዲሁም የመጠባበቂያ ግብአቶች እንዲመቻቹ ያደርጋል፣
11) ቢሮው በክልሉ የሚከሰቱ የወረርሽኝ እና ሌሎች የበሽታ ዓይነቶችን መረጃ ያሰባስባል ያሠራጫል፣

7. <u>የመማክርት ጉባዔ</u>
1) ተጠሪነቱ ለጤና ቢሮው ሆኖ የክልሉ የጤና ተቋሞች የጤና አገልግሎት ሽፋንና ጥራት እንዲሻሻል በሚደረገው ጥረት በአማካሪነት የሚያገለግል የመማክርት ጉባዔ ይቋቋማል፣
2) የመማክርት ጉባዔው አባላት በቢሮው ይሰየማሉ። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፣

8. <u>የሆስፒታሎች የሥራ አመራር ቦርድ</u>
1) እያንዳንዱ የመንግሥት ሆስፒታል ሕጋዊ ሰውነት በሚኖረው በሥራ አመራር ቦርድ ይመራል፣
2) የሥራ አመራር ቦርድ አወቃቀር ሆስፒታሉ እንደሚገኝበት አካባቢ የሚወሰን ይሆናል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፣
3) የሆስፒታሎች የሥራ አመራር ቦርድ አባላት አሰያየምና የሥራ ድርሻና ኃላፊነት በደንብ ይወሰናል፣

9. <u>የመሠረታዊ ጤና አገልግሎት አመራር</u>
1) የመሠረታዊ ጤና አገልግሎት ተቋማት አመራር ከተጠቃሚ ጎበረተሰብና ከጤና ተቋሙ በተውጣጡ ጥምር አካላት የሚዋቀር ይሆናል፣
2) የጥምር አካላት የሥራ ድርሻና ኃላፊነት እንዲሁም ተጠያቂነት በደንብ ይወሰናል፣

<u>ክፍል ሦስት</u>

<u>የጤና አገልግሎት የሚሰጥበት አኳኋን</u>

10. <u>የሙያ ሥነ-ምግባር</u>

ማንኛውም የጤና ባለሙያ፣ ወይም ድርጅት የሙያ ሥነ ምግባር መርሆዎችን የማክበር ግዴታ አለበት፣

11. <u>የሕሙማን አቀባበልና አላላክ ሥርዓት</u>
1) ማንኛውም የጤና ባለሙያ ወይም ተቋም በደረጃው የሚጠበቀውን የጤና አገልግሎት መስጠት አለበት፣
2) የጤና አገልግሎት ተጠቃሚዎች የሚፈልጉት የጤና አገልግሎት ዓይነት አጠቃቀም የጤና አገልግሎቱን አደረጃጀት የተከተለ ይሆናል። ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፣

3) ሕሙማን ከአንድ ጤና ተቋም ወደሌላ ሲላኩ የአላላክ ሥርዓትን የተከተለ ይሆናል፣
4) ሕሙማን የቅብብሎሽ ሥርዓትን ካልተከተሉ የመጣሻ ክፍያ እንዲከፍሉ ይደረጋል፤

12. <u>የግል ሕክምና መስጫ ዩኒት</u>

1) ሆስፒታሎች Â -@Â Èb!ÃãC የሆስፒታሉ wYM y-@Â Èb!ÃW አንድ አካል ሆኖ የሚሠራ የግል ሕክምና መስጫ ዩኒት ሊያቋቁሙ ይችላሉ፣
2) የግል ሕክምና መሰጫ ዩኒት አመራር አሠራርና አስተዳደርን በሚመለከት ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፣

<u>ክፍል አራት</u>

<u>የነፃ ሕክምና አሰጣጥ እና ክፍያ የማይጠየቅባቸው የጤና አገልግሎቶች</u>

13. <u>ነፃ ሕክምና አገልግሎት ተጠቃሚዎች</u>

1) የመክፈል አቅም የሌላቸው ስለመሆኑ የነጻ ሕክምና ማስረጃ የሚያቀርቡ ዜጎች በክልሉ በሚገኙ የመንግሥት የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ነፃ የጎክምና አገልግሎት ሊያገኙ ይችላሉ፣
2) የነፃ ሕክምና ማስረጃ የሚሰጥ ማንኛውም አካል ወይም ግለሰብ ለአገልግሎቱ የወጣውን ወጪ የሚሸፍን ይሆናል፣
3) የነፃ ሕክምና የሚሰጥበት ሥርዓትና ተጠቃሚዎች የሚለዩበት፣ ማስረጃና ወጪው በማንና እንዴት እንደሚሰጥና እንደሚሸፈን ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፣

14. <u>ክፍያ የማይጠየቅባቸው የጤና አገልግሎቶች</u>

የክልሉ መንግሥት የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማትና በጤና ኬላ የሚሠጡ አገልግሎቶችን ጨምሮ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የጤና አገልግሎቶች ያለክፍያ ይሰጣሉ፣

1) በመሰረታዊ የጤና አገልግሎት ተቋማት የሚሰጥ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት፣
2) በመሰረታዊ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት የሚሰጥ የቅድመ ወሊድ፣ የወሊድ እና የድህረ ወሊድ አገልግሎት፣
3) ፀረ-ስምንት የሕፃናትና እናቶች ክትባት፣
4) የሳንባ ነቀርሳ በሽታ ምርመራ ከተረጋገጠ በኋላ ክትትልና ሕክምና፣
5) በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ኤች-ኤይ-ቪ/ኤድስ ምርመራና ከእናት ወደ ፅንስ ኤች-አይ-ቪ/ኤድስ እንዳይተላለፍ መከላከል፣
6) የሥጋ ደዌ ሕክምና፣
7) ወረርሽኝ መከታተልና ቁጥጥር፣
8) ፊስቱላ፣
9) ለጤና ባለሙያዎች የሥራ አካባቢ ሥጋትን የሚያቃልሉ የክትባትና የሕክምና አገልግሎት፣
10) የቢጫ ወባ ክትባት፣
11) ወጪያቸው በመንግስት የሚሸፈን ሆኖ ወደፊት ያለክፍያ እንዲሰጡ በመመሪያ የሚወሰኑ ሌሎች የጤና አገልግሎቶች፣

<u>ክፍል አምስት</u>

<u>የክልሉ መንግሥት ሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች ፋይናንስ</u>

15. <u>የሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች የበጀት ምንጭ</u>

1) ከመንግሥት በጥቅል የሚመደብ በጀት፣
2) ከሚሰጡት የጤና አገልግሎት የሚያገኙት ገቢ፣
3) ከአገር ውስጠረና ከውጭ አገር በዓይነትና በጥሬ ገንዘብ የሚገኙ እርዳታዎች

4) ሌሎች የገቢ ምንጮች ይሆናል፣

16. <u>በገቢ ስለመጠቀም</u>

1) ሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች የሚያገኙት ገቢ በጤና አገልግሎት ተቋሙ ስም በተከፈተ ልዩ የባንክ ሂሣብ ውስጥ ተለይቶ ይቀመጣል፣
2) ሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች ከሚሰጡት አገልግሎት የሚያገኙት ገቢ ሙሉ በሙሉ በጥቅል ከሚመደብላቸው በጀት በተጨማሪ፣ ለሥራዎቻቸው ማስፈጸሚያ ይችላሉ፣
3) የሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ሥልጣን ባለው የመንግሥት አካል ኦዲት ይደረጋል፣

17. <u>የጤና አገልግሎት ክፍያ</u>

1) የሆስፒታሎች የሥራ አመራር ቦርድ ወይም የጤና ጣቢያዎች የሥራ አመራር የጤና አገልግሎት ክፍያ መጠን ለማሻሻል የሚያስችል ጥናት እንደአስፈላጊነቱ እንዲከናወን በማድረግ የውሣኔ ሀሳብ ለቢሮው ያቀርባል፣
2) ቢሮው ከየጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ሥራ አመራር ቦርድ ወይም የሥራ አመራር ተጠንቶ በሚቀርበው የአገልግሎት ክፍያ መጠን መሠረት ወጥ የሆነ ክፍያ መጠን ይወሰናል፣

18. <u>የዕቃና አገልግሎት ግዢ</u>

1) ሆስፒታሎች /ጤና ጣቢያዎች የዕቃና አገልግሎት ግዥ የሚፈጽሙት የመንግሥት የዕቃና አገልግሎት ግዥ መመሪያን በመከተል ይሆናል፣
2) በራሳቸው ሀብት፣ አመራርና አስተዳደር ለሆስፒታሉ/ጤና ጣቢያው ብቃት ያለው አገልግሎት መስጠት ለሚችሉ ባለሀብቶች ሆስፒታሎች /ጤና ጣቢያዎች ህክምና ነክ ያልሆኑ አገልግሎቶችን በውል መስጠት ይችላሉ፣
3) ሕክምና ነክ ያልሆኑ አገልግሎቶችን በውል ለግል ባለሀብት የመስጠት ሁኔታ የመንግሥት ዕቃ ግዢና አገልግሎት መመሪያን ተከትሎ ሊሰጥ ይችላል፣

19. <u>የጤና መድህን አተገባበር</u>

ቢሮው የተለያዩ መንግሥታዊ ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑና የግል ተቋማትና ህብረተሰቡ በጤና መድን የሚደራጁበትንና የሚጠቀምበትን ሁኔታ ያመቻቻል። ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፣

<u>ክፍል ስድስት</u>

<u>የመንግሥት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑና የግሉ ጤና ተቋም ዘርፍ ትብብር</u>

20. <u>የሥራ አካባቢን ስለማሻሻል</u>

ቢሮው የሙያ ሥነ ምግባርን የተከተለ የጤና አገልግሎት ለማረጋገጥ በፖሊሲ፣ በቴክኒክና በአሰራር ረገድ መንግሥታዊ ካልሆነ ድርጅትና ከግሉ ዘርፍ ጋር በቅንጅት ይሰራል፣

21. <u>መረጃን ስለማጠናከር</u>

1) የመንግሥት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑና የግሉ የጤና ተቋማት ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ስለበሽታዎች ዓይነት እና ሥርጭት ወቅታዊ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ማድረግ አለባቸው፣
2) ማንኛውም የጤና ተቋም የሚሰጠውን አገልግሎት በሚመለከት ዕለታዊና ወቅታዊ መረጃ የመያዝ፣ የማደራጀትና አስፈላጊ ሲሆን የማስተላለፍ ግዴታ አለበት።

<u>ክፍል ሰባት</u>

<u>የአስቸኳይ ጊዜ የጤና አገልግሎት</u>

22. በመንግሥት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና በግል የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት የሚሰጥ የአስቸኳይ ጊዜ የጤና አገልግሎት

1) ቢሮው በተፈጥሮና በሰው ሠራሽ ክስተቶች ምክንያት በሕዝብ ጤናና ሕይወት ላይ የሚደርሰውን አደጋ ለመከላከል እንዲቻል የመንግሥትን መንግሥታዊ ያልሆኑና የግል ጤና ተቋማት እና ሕሀረተሰቡን በማስተባበር የአስቸኳይ ጊዜ የጤና አገልግሎቶችን ያደራጃል፣ ያስተባብራል፣ ያስፈጽማል፣ ክትትል ያደርጋል።
2) ማንኛውም መንግሥታዊ ያልሆኑና የግል ጤና ተቋማት በወረርሽኝ እና ሌሎች አስቸኳይ የጤና አገልግሎት የመሳተፍ መብትና የመተባበር ግዴታ አለባቸው።
3) የአስቸኳይ ጊዜ የጤና አገልግሎት ክፍያን ተገልጋይ እንዲሸፍን አይጠበቅም፣

ክፍል ስምንት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

23. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1) የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስችል ደንብ ሊያወጣ ይችላል፣
2) የክልሉ ጤና ቢሮ ለአዋጁ አፈጻጸም የሚረዱ ዝርዝር መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፣

24. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

ይህንን አዋጅ የሚቃረን አዋጀ፣ ደንብ ፣መመሪያ ወይም ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

25. አዋጁ የሚጸናበት ቀን

ይህ አዋጅ በአፋር ክልል ዲንካራ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፣

2004 ዓ.ም
ሠመራ

እስማኤል አሊ ሴሮ

የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት

ርዕሰ መስተዳደር